# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 310 ሚያዝያ 10 2006


ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በህወሓት የጦር፣ የፓሊስና የስለላ መዋቅሮች ውስጥ የሕዝብ ወገኖች እንዳሉ ያውቃል። እነዚህ ወገኖቻችን እንደሌላው ሕዝብ ሁሉ - አንዳንዴም ከሌላው ባባሰ ሁኔታ - በፍትህ እጦት፣ በኑሮ መክበድና በዘረኝነት እየተሰቃዩ መሆናቸው ያውቃል። እነዚህ ወገኖቻችን ጥለው እንዲወጡ፤ ይህ ካልተቻለም ከውስጥ ሆነው የወያኔን የጦር፣ የፓሊስና የስለላ መዋቅሮች እንዲያፈራርሱ ጥሪ ያደርጋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ ህዝባዊ አመጽ እንዳሳሰበዉ ተናገረ

ሕወሃት መራሹ ወያኔ የግል ልሳኑ በሆነው የወያኔው ቴሌቪዥን አማካኝነት የሕዝብን አመጽና የራሱንም ስጋት (የቀለም አብዮት) በሚል ርእስ ማቅረቡ ታወቀ። የሌሎችን ሀገሮች ተሞክሮ በመጥቀስና አደገኛነቱን በማጉላት ለማስፈራራት የፈለገው ሕወሃት ለምን በዚህ ሰአት ይህ ፕሮግራም ማቅረብ እንዳስፈለገው ግን ለመግለጽ አልፈለገም።

ትላንትም ሆነ ዛሬ በማንኛውም ሰአት የአንዲት ሀገር ገዥዎች ስጋት የሕዝብ ጥያቄ እስካለ ድረስ ብቻ ነው የሚሉ አንዳንድ ታዛቢዎች የቀለም አብዮት ፕሮግራም ባሁኑ ሰአት የመተላለፉ ምክንያትም ባንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ከወትሮው በተለየ ጥንካሬና ድግግሞሽ እየታዩ ያሉት የሕዝብ አልገዛም ባይነትና አመጾች ሊሆኑ እንደሚችሉ አብራርተዋል።

ሕወሃት "እንኳንም ከእናንተ ተወለድን" እያለ የሚያሾፍበትና እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በከፍተኛ አፈና ስር ባለው የትግራይ ህዝብ ሳይቀር ከፍተኛ ጥላቻና ውግዘት እየደረሰበት ያለው ሕወሃት የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎት አሟልቶ አልቷል፣ ባሁኑ ሰአት የሕዝብ አመጽ ሊቀሰቅስ የሚችል ምክንያት የለም፤ የሕዝብ ጥያቄም የለም እያለ በተደጋጋሚ በተለያዩ የአገዛዙ ቁንጮዎቹ አማካኝነት ይልፈፍ እንጅ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ለማለት በሚያስደፍር መልኩ በሕወሃትና በሕወሃት ሰዎች የግለሰቦች እኩልነት ተጥሷል፣ የመናገርም ሆነ የመጻፍ መብት በወረቀት ላይ ከመቀመጡ በቀር በተግባር የለም፣ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ተንቀሳቅሶ ለመስራት አልተቻለም፣ የሀገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች ባለቤቶች በዓመት አንድ ጊዜ ከሚዘፈንላቸው በቀር እኩልነታቸውና ተፈላጊነታቸው የሰማይ እና የመሬት ያህል ሆኗል። የህ ሁሉ ታዲያ የሕዝብ አመጽ ለማስነሳት ከበቂ በላይ ነው የሚሉት ታዛቢ ሰሞኑን ያየነው የቀለም አብዮት ፕሮግራም ዓላማም ሕዝብን ማስፈራራት ቢሆንም መንስኤው ግን የሕዝብ አመጽ (የቀለም አብዮት) ስጋት ነው ይላሉ።

ከዘህ በፊት በዲላ፣ በአዋሳ፣ በጉጅና ነገሌ፣ በአጋዴን፣ በሀረር በደሴ፣ በጎንደር፣ በባህር ዳር፣ በአዲስ አበባ እንዲሁም በሌሎችም የሀገሪቱ አካባቢዎች በተደጋጋሚና በተለያዩ ጊዜያት ያየናቸው የሕዝብ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ የረቀቁ የስለላ መሳሪዎችን ለመግዛት ብዙ ገንዘብ እንደሚያባክን ታወቀ

ዴሞክራሲን ለመግደል፣ የመናገር ነጻነትን ለመገደብና የግለሰብ መብቶችን ለመጣስ ሕወሃት ከአንዳንድ የአውሮፓ ሀገሮችና ቻይና ገዝቶ እየተጠቀመበት ያለው እጅግ ዘመናዊ የስለላ መሳሪያ ለሰው ልጆች መብትና ለዴሞክራሲ ቆመናል በሚሉ አንዳንድ የአውሮፓ ሀገሮች ከፍተኛ ነቀፌታ እንደገጠመው ታወቀ። አልጀዚራ የተሰኘው የዜና አውታር እንደዘገበው ከሆነ ሕወሃት እጅግ ከፍተኛ በሆነ የውጭ ምንዛሪ ከእንግሊዝ፣ ከጀርመንና ከቻይና በመግዛት እየተጠቀመበት ያለውን እጅግ ዘመናዊ የስለላ መሳሪያ በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ጋዜጠኞችን፣ ፖለቲከኞችንና ለሰብአዊ መብት የሚታገሉ ግለሰቦችን ለመሰለል እየተጠቀመበት መሆኑን ማስረጃዎችን በመጥቀስ ዘግቧል።

ለዴሞክራሲ ቆመናል የሚሉትን የአሜሪካንና የእንግሊዝን ዝምታ ጭምር በመተቸት የሚጀምሩት እነዚህ ነቀፌታውን ያቀረቡ አንዳንድ የአውሮፓ ሀገሮች በየዓመቱ ከአራት ቢሊዮን ዶላር በላይ የእርዳታ ገንዘብ የሚያገኘው ሕወሃት ይህን ገንዘብ ከእርዳታ ውሉ ውጭ ዴሞክራሲን ለማፈንና መብትን ለመገፋፍ እየተጠቀመበት መሆኑን አጋልጠዋል። ስለሆነም በተለይም መሰሪያውን በመሸጥ ላይ ያሉ ሀገሮች ሽያጩን ለአምባገነን መንግስታት ከመሸጥ መቆጠብን ጨምሮ በዚህና ሌሎች ተመሳሳይ መሳሪያዎች ሽያጭ ላይ ልዩና አሳሪ ደንብ መጣል እንዳለባቸው አሳስበዋል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የጎሳ ግጭቱ ከከጉጂና ቦረና ወጥቶ ወደ ሌሎች ቦታዎች እየተዛመተ ነዉ

ባለፈዉ ሳምንት በቦረና ዞን መልካ ሶዳ ወረዳ ሃሎ ቀበሌ ዉስጥ ሁለት የጉጂ ተወላጆች ተገድለው መገኘታቸውን ተከትሎ የመልካ ሶዳ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ትምህርታዉን አቋመዉ ተቃውሟቸዉን ሲያሰሙ ዉለዋል። ተማሪዎቹ ከትምህርት ቤት በመውጣት ታፔላዎችን እየነቃቀሉ መጣላቸውን፣ የወረዳው አስተዳዳሪን መኪና በድንጋይ መሰባበራቸውን እንዲሁም አቶ ቡርቃ ደምቢ የተባሉትን የወረዳው የኢህዴድ መሰረታዊ ድርጅት አደራጅን መደብደባቸውን በስፍራው የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ።

ተማሪዎቹ ድርጊቱን ሲፈጽሙ የወረዳው ፖሊስ በተማሪዎች ላይ እርምጃ እንዳይወስድ ወላጆች ከፖሊስ ጋር ተፋጠው ለሰአታት ያሳለፉ ሲሆን፣ ማምሻውን የፌደራል ፖሊስ በብዛት በመምጣት አካባቢውን ተቆጣጥሯል። ተገድለው ከተገኙት መካከል አንዱ መምህር መሆኑም ታውቋል።ከነገሌ ቦረና ስያሜ ጋር በተያያዘ የተነሳው ግጭት ሌሎች ዞኖችንም እያዳረሰ መሄዱ ያሳሰባቸው ነዋሪዎች መንግስት ችግሩን ለመፍታት ያሳየውን ቸልተኝነት እየተቹ ነው። አገር ሽማግሌዎች ቀደም ብሎ ጉዳዩን ለመንግስት ሲያሳስቡ እንደነበር የሚገልጹት ነዋሪዎች፣ መንግስት በተለይም የክልሉ ርእሰ መስተዳድር በተለያዩ ጊዜዎች አቋማቸውን መቀያየራቸውን አሁን ለተፈጠረው ችግር መንስኤ ሆነዋል።

## ሰማያዊ ፓርቲ ታላቅ ህዝባዊ የተቃውሞ ሠልፍ ጠራ

ወያኔን በማስጨነቅ ላይ የሚገኘዉ ሠማያዊ ፓርቲ " ሰላማዊ ትግላችንን አጠናክረን በመቀጠል የተነጠቁ መብቶቻችንን እናስመልሳለን፡" በሚል ርእስ ትልቅ ሰላማዊ ሠልፍ አዲስ አበባ ዉስጥ መጥራቱንና የአዲስ አበባና የአካባቢዉ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ በሠልፉ ላይ እንዲካፈል ጥሪ ማድረጉን አሳወቀ። ፓርቲዉ የጠራዉን ሠላማዊ ሠልፍ አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ " ሰማያዊ ፓርቲ በመንግስት የሚፈጸሙ ሕገ ወጥ ድርጊቶች የሠብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥሰቶች እንዲቆሙ ለመንግስት አካላት በተደጋጋሚ ጊዜያት ጥሪ ቢያቀርብም የሚሰማው ማጣቱን ገልጿል።

በአገሪቱ የሚታዩ ችግሮች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ለማድረግ እሁድ ሚያዚያ 19/2006 ዓ.ም ከጠዋቱ 4 ሰዓት እስከ 8 ሰዓት የሚቆይ ከፓርቲ ጽ/ቤት እስከ ጃን ሜዳ የሚደርስ ታላቅ ህዝባዊ የተቃውሞ ሰልፍ ማዘጋጀቱን ፓርቲው በመግለጫው ጠቅሷል። የሠላማዊ ሰልፉን ቀንና ሰዓትም በአዋጅ ቁጥር 03198እ3 መሠረት ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ማሳወቁንም ገልጿል። በታላቁ ሕዝባዊ ሰልፍ ላይ መንግስት በእምነት ጣልቃ ገብነቱን እንዲያቆም፣ ዜጎችን ከቀያቸው ማፈናቀሉ እንዲቆምና የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ" የሚሉ ጥያቄዎች እንደሚነሱ የገለጸው ፓርቲው ፤ "ለገዢው ፓርቲ ስልጣን እንጅ ለህዝብ የማይጨነቅት ተቋማት በተለይ የውሃ፣ የመብራት፣ የቴሌ ኮሚኒኬሽንና የትራንስፖርት አገልግሎቶች ሕዝብን እያማረሩ በመሆናቸው በሠላማዊ ሠልፉ ላይ የሚነሱ ወሳኝ ጥያቄዎች ይሆናሉ" ብሎአል። የተነጠቁ መብቶቻችንን እናስመልስ ዘንድ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ሲቪክ ማህበራትና ሚዲያው ከሚደረገው ጥረት ጎን መቆም ሀገራዊ ግዴታ እንዲወጡ ፓርቲው ጥሪውን አስተላልፎአል።

## ወያኔ የ2007 ምርጫ ማሸነፊያ ስትራቴጂ ነድፎ አወጣ

ዉስጥ አዋቂ የሆኑ ምንጮች ለኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቭዥንና ሬድዮ በላኩት መረጃ መሰረት ወያኔ መጪዉን የ2007 ዓም ምርጫ ለማሸነፍ በሚያደርገዉ ጥረት ማስፈጸሚያ ለአርሶ አደሩ የማዳበሪያ እዳ እፎይታ በ2006/2007 የመኸር ምርት ዘመን የሚሰጥ ሲሆን፣ ለከተማ ነዋሪዎች ደግሞ በ20 ሺ ብር ቅድመ ክፍያ ለመኖሪያ ቤት ግንባታ የሚውሉ ቦታዎችን ይሰጣል። 20 ሺ ብር የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ለማቅረብ ለማይችሉት የከተማ ነዋሪዎች የምርጫ ቅስቀሳ በሚካሄድባቸው ወራት ከባንክ በብድር ገንዘቡን ለመልቀቅ እቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ገልጿል:: የቦታ መስጠት ሂደቱን በመላ ሃገሪቱ ተግባራዊ ለማድረግ የቦታ መረጣ አዘጋጅቶ መጨረሱንም ገልጿል::

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ይድረስ ለብዙሃኑ የሠራዊቱ አባል ወገናችን!!

የመከላከያ ሚኒስትር በተሰኘው የውሸት ሥልጣን ላይ የተቀመጠው አድርባይ ሲራጅ ፈርጌሳ ለይስሙላው ምክር ቤት ባቀረበው ሪፓርት፣ "የመከላከያ ሚኒስትር የብሔር ተዋጽዖ የተመጣጠነ" እንደሆነ ገለፀ። እንደ ሰውየው ሪፓርት ከሆነ የመከላከያ ሠራዊቱ 29.46 በመቶ አማራ፣ 25.05 በመቶው ከደቡብ ብሔሮች የተውጣጣ፣ 24.45 በመቶ አሮሞ፣ 17.47 በመቶው ትግራይ እና የተቀሩት ክልሎች ድርሻ 4.17 በመቶ ነው። መረጃው የተቀናበረው በክልል ቢሆንም የቀረበው ግን በዘር ነው። "ተመጣጠነ" የተባለውም የክልሎች ተዋጽዖ ሳይሆን የዘር ተዋጽዖ ነው። ሠራዊቱን እንዲህ በዘር ሸንሽንኖ የስታትስቲክስ ጨዋታ መጫወት አሳዛኝም አሳሳቢም ነገር ነው። የሆነ ሆኖ ይህ መረጃ፣ መረጃ ነው ተብሎ ለሕዝብ ቀርቧል።

ይህንን መረጃ የሰማ ማሰብ የሚችል አዕምሮ ያለው ሰው የሚጠይቀው የመጀመሪያ ጥያቄ "የሠራዊቱ ስብጥር በተገለፀበት ዓይነት የመኮንኖቹም ስብጥር ለምን አልተገለፀም?" የሚል ነው። ይህ ጥያቄ በአስተዋይ ሰው አዕምሮ ውስጥ በተነሳነበት ፍጥነት ምላሽ ያገኛል፤ ምክንያቱም ምላሹ እዚያው እቁጥሮቹ ውስጥ አለ። የመኮንኖቹ ስብጥር ያልተነገረበት ምክንያት አብዛኞቹ መኮንኖች በ17.47 በመቶው በመሆናቸው ነው። ወደዚህ መምደሚያ የሚደርሰው አሳቢው ስለፈለገው ሳይሆን የመረጃው አቀራረብ አመክኖ (ሎጂክ) ወደዚያ ስለሚገፋ ነው። በዚህም ምክንያት በሲራጅ ፈርጌሳ አንባቢነት የቀረበው የህወሓት ሪፓርት በገዛ ራሱ ላይ ነው የተኮሰውም።

እኛ እንደ ሲራጅ ፈርጌሳ የዘር ስታትስቲክስ ውስጥ አንገባም፤ መልዕክታችን ለተገፋውና እየተበደለ ላለው ለመላው የሠራዊቱ አባል ነው።

ይድረስ ሹመትና ኃላፊነት ተነፈገህ፤ የጥቂቶቹን ሀብትና ዝና ጠባቂ እንድትሆን ለተፈረደብህ ወገናችን!!! እስከመቼ ለህወሓትና ጥቂት አጎብዳጅ መኮንኖች ባርነት ትገዛለህ? ይህ ውርደትህ የሚያበቃው መቼ ነው? የታጠቀው መሣሪያ የአገርህና የራስህ ክብር ማስጠበቂያ፤ ነፃነትህን መጎናፀፊያ የምታደርገው መቼ ነው? ለመሆኑ ለመኮንንነት የሚያበቃ ጭንቅላት፣ ልምድ ወይም እውቀት ከፓርቲ አባልነት ነው የሚገኘው? ህወሓቶችና አጋሮቻቸው በሠራዊቱ ያሉትን ቁልፍ ኃላፊነቶችን ሁሉ ጠቅልለው ይዘው "ጀሌዎቻችን እንዲሆኑ ፈቅደንላቸዋል" የሚል ሪፓርት የሚያቀርቡት ምንኛ ቢንቁን ነው? ይህንን ውርደት ኢትዮጵያዊው ወኔህ እንዴት ይቀበለዋል?

ኢትዮጵያዊው ወታደር ከሌላው ኢትዮጵያዊ በባሰ በአምባገነንና ዘረኛ አለቆቹ እየተዋረደ እንደሆነ በገሃድ የሚታይ ጉዳይ ነው። የህወሓት አባላት ቁልፍ የስልጣን ቦታዎችን ይዘው ጦር ሠራዊቱን እንደ ፓርቲ መዋቅር ሲመሩት ማየት የሠራዊቱን አባላት ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚያንገበግብ ጉዳይ ነው። ሠራዊቱ አገርና ሕዝብን ሊጠብቅበት ይገባ የነገረው መሣሪያ በንጹሃን ዜጎች ላይ እንዲያነሳ፤ ሰላማዊ ሰዎችን እንዲደበድብ፣ እንዲረግጥና እንዲገድል የሚያዙት እነዚህ የህወሓትና ጥቂት አጎብዳጅ አለቆቹ እንደሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃል። ሆኖም የኢትዮጵያ ወታደር የታዘዘው ሁሉ የሚፈጽም ባርያ አይደለምና በእነዚህ ጥቂት ዘረኛ አለቆችህ ላይ እንዲነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠይቃል።

ውድ የኢትዮጵያ ወታደር ሆይ!!! "ዘረኛነት በቃኝ" በል። ለነፃነት፤ ለእኩልነት፤ ለአገር ክብር በሚታገሉ ወገኖችህ ላይ ክንድህን አታንሳ። የጥቂት ዘረኞችን ሥልጣን በማራዘም ከሚመካበክ የኢትዮጵያ ድሃ ሕዝብ ጋር ዘላቂ ቂም ውስጥ አትግባ። በትእቢት "ሁልሽንም ረግጠን እንገዛለን" ብለው የሚፎክሩት አንተን ከወገንህ ጋር ደም በማቃባት ነውና "እምቢ!" በላቸው። ለዘረኞች ስልጣን ብለህ አትሙት! እንዲያውም ለገዛ ራስህ ክብር፣ ለቤተሰቦችህና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ግንባር ቀደም አርበኛ ሁን።

ከላይ የተባለው ለፓሊስ አባላትም ይሠራል። በህወሓትና ህወሓት በየቦታው በፈጠራቸው ጀሌዎች የሚመራ በመሆኑ ከሕዝብ ፍላጎት በተፃፃሪ የቆመ ይምሰል እንጂ የኢትዮጵያ ፓሊስ የሕዝብ ወገን እንደሆነ በተለያዩ አጋጣሚዎች የታየ ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍትህ እጦት የሚሰቃየውን ያህል ብዙሃኑ ፓሊስ በፍትህ እጦት እየተሰቃየ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ጫና እንዳዳከመው ሁሉ የኢትዮጵያ ፓሊስም ኑሮ ከብዶታል። እንደሌላው ሰው ሁሉ ፓሊስንም ዘረኝነት አስመርሮታል። ብዙሃኑ ፓሊስ አቅሙን በጥቂት አምባገነን አለቆቹ ላይ የሚፈትሽበት ጊዜ ደርሷል።

የስለላ ተቋማቱ ጉዳይ ለየት ይላል። "ደህንነት" ተብሎ በሚሞካሸው የጆሮጠቢዎች ስብስብ በሆነው መሥሪያቤት እና በኤክትሮኒክስ ብርበራ የተሠማሩ "ባለሙያ ጆሮ ጠቢዎች" ውስጥ ህወሓት በአለቃነትም በምንዝርነትም አብዛኛውን ቦታ ይዟል። ሆኖም እዚህም የሕዝብ ወገኖች እንዳሉ ይታወቃሉ። በእነዚህ ቦታዎች ያላችሁ የሕዝብ ወገኖች ሲቻል በገሃድ ሳይቻል በሚስጥር ተቋማቱን የማዳከም ሥራችዎችን መሥራት የህሊናና የዜግነት ግዴታችሁ ነው። ከእናንተ ብዙ፤ እጅግ ብዙ ይጠበቃል። የምታሾልኳት ትንሿ መረጃ የብዙዎችን ሕይወት ልትታደግ ትችላለች፡

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በህወሓት የጦር፣ የፓሊስና የስለላ መዋቅሮች ውስጥ የሕዝብ ወገኖች እንዳሉ ያውቃል። እነዚህ ወገኖቻችን እንደሌላው ሕዝብ ሁሉ - አንዳንዴም ከሌላው በባሰ ሁኔታ - በፍትህ እጦት፣ በኑሮ መክበድና በዘረኝነት እየተሰቃዩ መሆናቸው ያውቃል። እነዚህ ወገኖቻችን ጥለው እንዲወጡ፤ ይህ ካልተቻለም ከውስጥ ሆነው የወያኔን የጦር፣ የፓሊስና የስለላ መዋቅሮች እንዲያፈራርሱ ጥሪ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ ህዝባዊ አመጽ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አመጾች ምንም እንኳ በገዥው ቡድን ታጣቂዎች በጉልበት ይጨፍለቁ እንጅ ያስተላለፉት መልክትና በሕወሃት ላይ ያሳደሩት ስጋት ከፍተኛ ነበር። ስለሆነም ምናልባት ይህን የመሰሉና ጠንካራ የሕዝብ አመጾች ቢነሱ እንዴት መቆጣጠር ወይም ማፈን እንችላለን በማለት ሕወሃት በከፍተኛ ሁኔታ ሲሰራ ቆይቷል የሚሉት ሌላው ታዛቢ ደግሞ "ሕወሃት ያልተገነዘበው ግን እንዲህ አይነት ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎችን ለማጥፋት ብቸኛው ዘዴ ሕዝብ እያቀረበው ያለውን ጥያቄ መመለስ ብቻ መሆኑን ነው" ይላሉ። ይህን ማድረግ እስካልቻለ ድረስና በየጊዜው ጥያቄዎችን በማፈን እቀጥላለሁ ካለ ግን "ሕዝብን እስከመጨረሻው አፍኖ ማስቀረት ስለማይቻል፤ ላንድ በሽታ መድሃኒት መውሰድ ጀምሮ እንደማቋረጥ ያለ ነው። ምክንያቱም በሽታው በድጋሚ ሲነሳ ከበፊቱ ይበልጥ ተጠናክሮ ነውና የሚመጣው" ይላሉ።

ሕወሃት የሕዝብ ጥያቄዎችን በጉልበትና በአፈና በመጨፍለቅ ላለፉት የአገዛዙ ዘመናት ይቀጥል እንጅ ጥያቄዎችን ግን ከናካቴው ሊያቆማቸው አልቻለም። ይባስ ብሎ የሕዝብ ጥያቄዎች መሰረተ ሰፊ እየሆኑና ሕብረ ብሔራዊ ምልክ እየያዙ መምጣታቸው ነው በሰፊው የሚነገረው። አንዴውም ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው አንዳንድ ታዛቢዎች እንደሚሉት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎችና በተደጋጋሚ የተቀሰቀሱት እነዚህ የህዝብ ጥያቄዎችና ያስከተሉት የሕዝብ አመጽ ተቀናጅተው ተከናውነው ቢሆን ኖሮ ሕወሃት መራሹ ወያኔ እስካሁን ታሪክ ሆኖ ነበር ካሉ በኋላ አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄና የሕዝብ አመጽ ተቀናጅቶ እስከተከናወነ ድረስ ወያኔን ለማስወገድ በጣም ከባድ አይደለም ምክንያቱም ሕወሃት መራሹ ወያኔ መሰረት የሌለው ከላይ ብቻ የተንሳፈፈና በሃይሉ ብቻ የሚተማመን ስብስብ ነውና። ለአብነትም ከ1997 ሀገራዊ ምርጫ በኋላ ተከስቶ በነበረው ሀገራዊ የሕዝብ አመጽ ምን እንደተከሰተ ማስታወስ ብቻ ሕወሃት ባዶ መሆኑን ለመገንዘብ በቂ ነው። የሰሞኑ የወያኔው ቴሌቪዥን የቀለም አብዮት ዝግጅትም ይህን የሕዝብ አመጽ ከመፍራት የመጣና ከወዲሁ ሕዝብን ለማስፈራራት የታሰበበት ነው" በማለት ያጠቃልላሉ።

የሕዝብ ጥያቄ በመኖሩ ምክንይት ተፈጠርኩ እያለ ስለ ራሱ በተደጋጋሚ የሚያወራው ሕወሃት ላፉ ያህል ያካድ እንጅ ባሁኑ ሰአት በጣም ከበቂ በላይ የሕዝብ ጥያቄዎች እንዳሉ አሳምሮ ያውቃል። ይህ እውነታም ነው ይህን የቀለም አብዮት ዝግጅት እንዲያዘጋጅ ያስገደደው የሚለው የብዙዎቹ እምነት እንደሆነ በሰፊው እየተነገረ መሆኑ ታውቋል።

## ግድብ እያፈረሱ ጎርፍ መከላከል አይቻልም !!!

ዘረኛዉ የወያኔ ዘገዛዝ በ2002 ዓም “አኬልዳማ” የዛሬ ሁለት አመት ደግሞ “ጂሀዳዊ ሀረካት” የሚባሉ ሁለት አስጸያፊ ድራማዎችን ሰርቶ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማታለል የሞከረዉ ወያኔ በያዝነዉ ሳምንት መግቢያ ላይ ደግሞ ሌላ “የቀለም አብዮት” የሚባል ቂላቅል ድራማ ሰርቶ ለለዉጥ የተዘጋጀዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ቀለብ ለመስለብ ጉድ ጉድ ማለት ጀምሯል። ይህ በኪነጥበብ የፈጠራ ስራዉ ሳይሆን እንደማም ቂሎ በተፈጥሮዉ አስቂኝ የሆነ የዉሸት ድራማ የሚያሳየን ወያኔ በስልጣን ላይ ለመቆየት የማያደርገዉ ምንም ነገር አለመኖሩን ብቻ ነዉ። ይህንን ድራማ ከአኬል ዳማና ከጅሀዳዊ ሀረካት የሚለየዉ አንድ ነገር ቢኖር በዚህ ድራማ ዉስጥ ዋና ዋናዎቹ ተዋናንያን የተለመዱት የኢቲቪ ካድሬዎች ሳይሆኑ ሳይማሩ ምሁር የሚል ስያሜ የተሰጣቸዉ ሁለት ወጣት ካድሬዎችና የዉሸት እመቤት በመባል የምትታወቀዉ አዛዉንቷ እሚሆይ ሚሚ ስብሀቱ መሆናቸዉ ብቻ ነዉ።

ወያኔ በአኬልዳማ ድራማ ጥላሸት ለመቀባት የሞከረዉ ግንቦት ሰባትን የመሳሰሉ ለኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ለህዝቦቿ መብት መከበር በህይወታቸዉ የቆረጡትን የህዝብ ወገኖች ሲሆን፤ ጅሀዳዊ ሀረካት ደግሞ የአገርና የህዝብ ጠላት አድርጎ የሚያቀርበዉ የማምለክ መብታችን ይከበር ብለዉ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ያቀረቡትን የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮችን ነዉ። እንደተለመደዉ በዉሸት ታጅቦ ከሰሞኑ ብቅ ያለዉ ሦስተኛዉ የወያኔ ድራማ ደግሞ ከ85 በመቶ በላይ የሚያወራዉ ስለኢትዮጵያ ሳይሆን ዩክሬይን፤ ጆርጂያ፤ ሰርቢያና ኪርግስታን ዉስጥ ስለተካሄዱት ህዝባዊ የለዉጥ እንቅስቃሴዎችና ስለቀድሞዉ የቬኑዝዌላ መሪ ስለ ሁጎ ሻቬዝ ነዉ። የድራማዉ አቢይ መልዕክት ደግሞ የቀለም አብዮት ልማትን የሚጻረርና አገርን የሚጎዳ ስለሆነ ኢትዮጵያ ዉስጥ መሞከር የለበትም የሚል ነዉ። በዚህ የሞኞች ድራማ ዉስጥ ምሁርና ተንታኝ ሆነዉ የቀረቡትን የጂማ ዩኒቨርሲቲዉን መርከብ ነጋሽንና የኢትዮጵያ አለም አቀፍ የሰላምና የልማት ኢንስቲትዩት ባልደረባ የሆነዉን አቤል አባተን አደብ ገዝቶ የተከታተለ ሰዉ እነዚህ ወያኔዎች ሌላ ቢቀር የተማረ ሰዉ አጠገባቸዉ የለም እንዴ የሚያሰኙ ብዙ ነገሮችን መታዘብ ይችላል። በእርግጥም መርከብና ነጋሽና አቤል አባተ ኢትዮጵያ ዉስጥ ጭነት የተሸከመዉን አህያ እየመራ ወደ ገበያ የሚወስደዉ ገበሬዉ ሳይሆን በተቃራኒዉ ገበሬዉን እየመራ ወደ ገበያ የሚወስደዉ አህያዉ መሆኑን በማያወላዳ መልኩ አሳይተዉናል። እነዚህ ሁለት በጥንቃቄ ተመርጠዉ የመጡ የወያኔ ካድሬዎች እንዲህ ነበር ያሉት ።

በድራማዉ የመጀመሪያ ክፍል ዉስጥ የቀለም አብዩት ምዕራባዉያን መንግስታት በታዳጊ አገሮች ዉስጥ ጣልቃ ለመግባት የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነዉ እንጂ የህዝብ ምሬት የወለደዉ ወይም አገር በቀል ክስተት አይደለም ሲሉ የከረሙት ምሁር ተብዬዎቹ መርከብ ነጋሽና አቤል አባተ በድራማዉ የመጨረሻ አካባቢ በማንኛዉም አገር ዉስጥ ሙሰኝነት ከነገሰ፤ ህብረተሰቡ ያለዉን መንግስት ዬኔ ነዉ ብሎ ካላመነ፤ ህዝብ በዲሞክራሲ ሂደቱ ዉስጥ ካልተሳተፈ፤ የፖለቲካዉ ስርዐት አግላይ ከሆነና በብሔራዊ ኤኮኖሚዉ ተጠቃሚ የሚሆኑት ጥቂቶች ብቻ ከሆኑ የቀለም አብዮት መከሰቱ አይቀርም እያሉ እራሰቸዉን የተናገሩትንቃል እራሳቸዉ መልሰዉ ሲያፈርሱት ይታያሉ። እነ አቤል አዞረዉ የማያዩ ጋሪ ፈረሶች ስለሆኑ ነዉ እንጂ እነዚህ አብዮት ያስሳሉ ያሏቸዉ ነገሮች ሁሉ ኢትዮጵያ ዉስጥ በግልጽ የሚታዩ ነገሮች ናቸዉ።

የእነዚህ ሁለት የወያኔ ቡችላዎች ጉድ በዚህ ብቻ አያበቃም። የሩሲያዉን አምባገነን ቪላድሚር ፑቲንንና ሟቹን የቬኑዝዌላ ፕሬዚዳንት ሁጎ ቻቬዝን እንደ ህዝብ መብት ተሟጋች ብሄራዊ ጀግና አድርገዉ ስስሏቸዉ ይታያሉ። ባጠቃላይ ይህ ምስቅልቅሉ የወጣ የወያኔ ድራማ በአንድ በኩል ኢትዮጵያ ምዕራባዉያን መንግስታት ለቀለም አብዮት የሚያስቧት አገር መሆኗን ይናገርና፤በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ዉስጥ የምዕራባዉያን የቀለም አብዮት ያልተሳካዉ እንደ ሌሎቹ አገሮች ለምዕራባዉያን የሚታዘዙና በሙሰኝነት የተጨማለቁ መሪዎች ባለመኖራቸዉ ነዉ ይላል። መቼም የወያኔ መሪዎች ሙሰኞች አይደሉም ሲባል እንኳን አንጡራ ኃብቱን የተዘረፈዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዘራፊዎቹ የወያኔ መሪዎችም ቢሆኑ እዉነት ነዉ ብለዉ የሚቀበሉ አይመስለንም። ኢትዮጵያ ሙሰኝነት የነገሰባት አገር ናት፤ ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት እፍኝ የማይሞሉ የትግራይ ልህቃን ናቸዉ። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በጉጂና በጌዲኦ፤ በቦረናና በጋሪ ወይም በኦሮሞና በጉሙዝ ብሄረሰቦች መካከል ግጭት ተፈጠረ ሲባል የተለመደ ነገር ነዉና የሚደነግጥ ሰዉ የለም። እንግዲህ እንደዚህ አይነቱን አፍንጫቸዉ ስር በየቀኑ የሚፈጸመዉን በደል ማየት የተሳናቸዉ ሚሚ ስብሀቱ፤ አቤል አባተና መርከብ ነጋሽ ናቸዉ በአስር ሺዎች ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሰለሚገኙ አገሮች ሙሰኝነትና የብሄር ብሄረሰቦች ግጭት የሚነግሩን . . . ለካስ “ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነዉ” የሚሉት ተረት አለምክንያት እልተተረተም።

የወያኔ ፍርፋሪ ሆዳቸዉን ሞልቶ አይናቸዉን የሸፈነባቸዉ አቤል አባተና መርከብ ነጋሽ ቁልጭ ብሎ የሚታይ እዉነት ተሰዉሮባቸዉ ነዉ እንጂ የወያኔ አገዛዝ በነፃ ገበያና በሶሻሊዝም መካከል ግራ ገብቶት የተገተረ የምዕራባዉያን የቤት ዉስጥ ሰራተኛ ነዉ። ምዕራባዉያንም ቢሆኑ ወያኔ ሠላማዊ ሠልፈኞችን በጥይት ሲጨፈጭፍና ህዘብን እያሰረ ሲያንገላታ አፋቸዉን ዘግተዉ የሚመለከቱ የወያኔ የእንጀራ አባቶች ናቸዉ። የወያኔ መሪዎች የምዕራባዉያን የገንዘብና የዲፕሎማሲ ከለላ ባያገኙ ኖሮ ዛሬ እነሱም እንደ ደረግ አባላት ቦታቸዉ ስደት ወይም እስር ቤት ይሆን ነበር።

ለመሆኑ ለምንድነዉ የአምባገነን መሪዎች እርግጫ፤ አስርና ግድያ ሰለባ የሆኑት የአዉሮፓ፤ የኢሲያና የአፍሪካ ህዘቦች እራሳቸዉን ከአምባገነኖች ቀንበር ለማላቀቅ የሚያደርጉትን ሰለማዊ ትግል ወያኔ እንደ ወንጀል የሚመለከተዉ? ደግሞስ ዩክሬን፤ ሰርቢያ፤ ጆርጂያና በሌሎችም አገሮች ዉስጥ የተካሄዱት ሠላማዊ የቀለም አብዮቶች ሁሉ ደም ያፋሰሱ ፀረ ህዝብና ፀረ አገር እንቅስቃሴዎች ከሆኑ ወያኔ ዬትኛዉን የትግል ስልት ይሆን “ሠላማዊ ትግል” ብሎ የሚጠራዉ? መደራጀት፤ መሰብሰብና ሀሳብን በነፃነት መግለጽ ሽብርተኛ ካሰኘ፤ በሰላማዊ መንገድ መታገል እንደ ወንጀል ከታየ ወያኔ ህጋዊ የትግል ስልት ነዉ ብሎ የፈቀደዉ ዬትኛዉን የትግል ስልት ነዉ? ወይስ ወያኔ እየነገረን ያለዉ ረግጬ እገዛችኋላሁ፤ አፋችሁን ዘግታችሁ ተገዙ ነዉ።

“የቀለም አብዮት” የሚል ስያሜ የተሰጠዉ የሰሞኑ የወያኔ ድራማ የሚጀምረዉ በጠመንጃ ድምጽና በእሳት ቃጠሎ ነዉ። ይህ ደግሞ የቀለም አብዮት ሠላማዊ አለመሆኑን ለማሳየት ሆን ተብሎ የተሰራ የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ነዉ።_ለመሆኑ የ1997ቱን የወያኔ ጭፍጨፋ ጨምሮ ከሰርቢያ እስከ ዩክሬን ፤ ከቱኒዝያ እስከ ግብፅ በተካሄዱት ሠላማዊ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ታንክና የታጠቀ ኃይል እየላከ ደም ያፋሰሰዉ ህዝብ ነዉ ወይስ የየአገሩ አምባገነን መሪ? “ዘር ከልጓም ይስባል” ነገር ሆኖባቸዉ በዘር ተስበዉ በአንድ ወቅት ያይ የነበረዉመን አይናቸዉን አሳዉሮት ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ እናቱ ላይ ቁጢጥ ብለዉ የሚረግጡትን ጨካኝ አምባገነኖች ማባረር ወይም ማስወገድ የተፈጥሮ መብቱ መሆኑን ለእሚሆይ ሚሚ ስብሀቱ ማን በነገራቸዉ?። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ይህንን የህዝብ የተፈጥሮ መብት እየተዋጉ ነዉ የአገርንና የህዝብን ደህንነት ለማስከበር የማናደርገዉ ምንም ነገር የለም እያሉ በህዝብና በአገር ላይ የሚዘብቱት። ህዝብን በጅምላ አስረዉ ሰቆቃ እየፈጸሙና ሠላማዊ ዜጎችን በዉድቅት ሌሊት ከመኖሪያ ቤታቸዉ ጎትተዉ በጥይት ደብድበዉ እየገደሉ የህዝብን ደህንነት ለማስከበር ነዉ ብለዉ ቢነግሩን እየዋሹ አድገዉ እየዋሹ ያረጁትን የወያኔ መሪዎች ቀርቶ የሰማይ መልዐክትንም አናምናቸዉም።

በቀለም አብዮት ድራማ ዉስጥ ሌላም አንድ እጅግ በጣም የሚገርምም የሚያሳዝንም በወያኔ ተራ ዉሸትና አዉቃለሁ ባይነት የተጀቦነ ድንቁርና አለ። እሱም በእዉቀት አልባ ጭንቅላታቸዉ የሚታወቁት ተራዎቹ የወያኔ ካድሬዎች ቀርቶ ልህቃን ነን ባዮቹም በሚገባ ያልተገነዘቡት ነገር ግን በነጋ በጠባ ሊተነትኑት የሚሞክሩትና እንዳላዋቂ ሳሚ በነጋ በጠባ ቆሻሻ የሚቀቡት የሊብራል ፍልስፍና አስተሳሰብ ነዉ። የወያኔ ካድሬዎች እንዲያዉቁት የምንፈልገዉ አንድ ቁም ነገር ቢኖር ሊብራሊዝም ወይም የልብራል ፍልስፍና ወያኔዎች እንደሚያመልኩበት እንደ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ደደቢት በረሃ ዉስጥ ለዚያዉም በዘረኝነት በተጨማለቀ ሰዉ ተጽፎ መክኖ የቀረ የመላ መላ ድርሰት አይደለም። ይልቁንም ሊብራሊዝም በመቶዎች በሚቆጠሩ አመታት ዉስጥ በተለያዩ ሊቃዉንት እየዳበረ የመጣና አሁንም በመደባር ላይ የሚገኝ ህያዉ ፍልስፍና ነዉ።

በመሰረቱ ሊብራሊዝም በወያኔዎች መንደር ሌላ አዲስ ትርጉም ካልተሰጠዉ በቀር በሦስቱ የመንግስት አካላት መካከል የስልጣን ክፍፍልና ልዩነት መኖር አለበት የሚል፤ በእኩልነት፤ በነፃነት ፤ በሰብአዊ መብቶች፤ በነፃ ሜድያ፤ ነፃ ምርጫ፤ ነፃ ገበያና በግል ኃብት ዙሪያ እጅግ በጣም ጠንካራ አቋም ያለዉና እነዚህ መብቶችና ነፃቶች መከበር አለባቸዉ የሚል የፖለቲካና የኤኮኖሚ ፍልስፍና ነዉ። ሀሳበቸዉን በነፃነት የመግለጽ መብት የሌላቸዉ ጥራዝ ነጠቆቹ የወያኔ ካድሬዎች ምን እንደሆነ እንኳን የማያዉቁትን ሊብራል ፍልስፍናን የሚያወግዙት ሆዳቸዉን ለመሙላት ሲሉ ነዉ እንጂ የሊብራሊዝም ፍልስፍና ቢገባቸዉና ቢረዱት ኖሮ ትግላቸዉ ከወያኔ ጋር ይሆንና ሆዳቸዉንም አዕምሯቸዉንም መሙላት ይችሉ ነበር። ምንግዜም ቢሆን ሊብራልዝምና አብዮታዊ ዲሞክራሲ ፊቱ ላይ ቀርቦለት ሊብራሊዝምን አዉግዞ አብዮታዊ ዲሚክራሲን የሚያወድስ ለሰዉ ልጆች በጎ ነገር አስቦ የማያዉቀዉ ሳጥናኤል ብቻ ነዉ። ወያኔንም ከሳጥናኤል ተርታ የምንመድበዉ ልክ እንደ ጌታዉ እንደ ሳጥናኤል ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድም ቀን በጎ ነገር አስቦ ሰልማያዉቅ ነዉ።

ሊብራሊዝም ወይም የሊብራል ፍልስፍና አገሮች አታሪካዊ አመጣጣቸዉን፤ ባህላቸዉንና የሚገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታ እያጤኑ ለክተዉ የሚለብሱት ልብስ ነዉ እንጂ በአንድ ወጥ ተሰፍቶ እየተነቀለ የሚተከል የእድር ድንኳን አይደለም። ለምሳሌ ብዙዎቹ የአዉሮፓ አገሮች፤ አሜሪካ ፤ ህንድ፤ አዉስትራሊያና ደቡብ አፍሪካ የሊብራል ፍልስፍናን የሚከተሉ አገሮች ናቸዉ፤ ሆኖም የእያንዳንዱ አገር ፖሊቲካና ኤኮኖሚ በዚህ ፍልስፍና ይመራ እንጂ የተዋቀረበት መንገድ ይለያያል። የወያኔ ጀሌዎች ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት መሪዉ እኔ ካልሆንኩ ክልሉ የራሱን እድል በራሱ ይወስናል አሉ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በሶማሌ ክልል የሚፈጸመው ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት በክልሉ ያሉትን ባለስልጣኖች ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የኢህአዴግን ባለስልጣኖችን በአለማቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት የሚያስጠይቅ መሆኑ በግልጽ የገባዉ ወያኔ የሶማሌዉን ክልል ፕሬዚዳንት አብዲ ሞሃመድ ኡመርን ለማውረድ እንቅስቃሴ መጀመሩ አስመልክቶ አዝማሚያዉ ያላስደሰታቸዉ የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት "እኔ ከስልጣን የምነሳ ከሆነ የሶማሌ ክልል የራሱን እድል በራሱ ይወስናል ሲሉ ተናገሩ።

ወያኔ አንዳንድ እጃቸውን ከሰጡና በሃይል ታፍነው ከተወሰዱ የቀድሞ የኦብነግ አመራሮች ጋር የጀመረው ቅርርብ ያላስደሰታቸዉ አቶ አብዲ የእርሳቸው ታማኝ ደጋፊ የሆኑ በውጭ አገራት የሚኖሩ የክልሉን ተወላጆች ጅጅጋ ውስጥ በሰበሰቡበት ወቅት ፣ እርሳቸው ከስልጣን የሚወርዱ ከሆነ፣ ክልሉ የእራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል የሚለውን የህገመንግስት አንቀጽ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ዝተዋል።

አቶ አብዲ የተናገሩትን ነገር ለማስፈጸም ምን ያክል ኃይልና ስልጣን እንዳላቸዉ ብዙ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም በእርሳቸውና በተወሰኑ የህወሃት ጄኔራሎች የሚመራ ልዩ ሚሊሺያ የሚባል ሰራዊት ማቋቋማቸው የሚታወስ ነዉ።ይህ በእንዲህ እንዳለ ታላቁዋን ሶማሊያን ለመመስረት አላማ ይዞ ሲንቀሳቀስ ለነበረው ሙህመድ አብዱላህ ሃሰን በጅጅጋ ከተማ የተሰራው ሃውልት ተመርቋል። በቅኝ ግዛት ዘመን ለታላቁዋ ሶማሊያ መመስረት ሲታገል የነበረው ሙህመድ ሃሰን ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ተከታታይ ጦርነት አድርጎ ነበር። የክልሉ መንግስት የኢትዮጵያን አንድነት የማይፈልገውንና ለታላቁዋ ሶማሊያ መመስረት ሲታገል ለነበረው ሰው ሃውልት ማቆሙ ብዙዎችን ያስገረመ ክስተት ሆኗል። ሙሃመድ ሃሳን በሞቃዲሾ ከተማም እንዲሁ ታላቅ ሃውልት ተገንብቶለታል።

## በአማራ ክልል በወያኔ አገዛዝ ላይ የሚደገዉ ተቃዉሞ እየጨመረ መምጣቱ ታወቀ

በሰሜን ጎንደር ዞን ጭልጋ ወረዳና በአካባቢዉ የሚኖሩት የቅማንት ብሄረሰብ አባላት ካነሱት የማንነትና የአስተዳደር ጥያቄ ጋር ተያይዞ አይከል ከተማ ዉስጥ ተማሪዎች ባካሄዱት የተቀዉሞ ሰላማዊ ሠልፍ ከፖሊስ ጋር ግጭት ተፈጥሮ ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ሰዎች በአድማ በታኝ ፖሊሶች ተደብድበው ጉዳት እንደደረሰባቸው ሰሜን ጎንደር ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ።ግጭቱ የተፈጠረዉ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የተዉጣጡ አባላት ወደ አካባቢው ሄደዉ የተለያዩ መጠይቆችን በማድረግ ብሄረሰቡ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ይሰጣሉ ተብሎ እየተጠበቀ ባለበት ወቅት መሆኑ ጉዳዩን ይበልጥ አወዛጋቢ አድርጎታል። ነዋሪዎች ይገልጻሉ።

ፌዴሬሽኑ ጥናት በሚያደርግበት ወቅት ህዝቡን ታስተባብራላችሁ የተባሉ ከ68 ያላነሱ ሰዎች ከአካባቢያቸው ርቀው እንዲታሰሩ ተደርጓል። ከታሰሩት መካከል መምህራን የሚገኙበት ሲሆን፣ ለተማሪዎች ተቃውሞ መንስኤ የሆነውም የመምህራኖቻቸው ደብዛ መጥፋት ነው። ተማሪዎቹ የታሰሩት የብሄረሰቡ መሪዎች ካልተፈቱ ትምህርት አንማርም በማለት ካለፉት ሶስት ቀናት ጀምሮ ሲያካሂዱት ነየነበረው ተቃውሞ ዛሬ ወደ ግጭት አምርቶ በርካታ ተማሪዎች እና የአይከል ከተማ ነዋሪዎች እንደተደበደቡና እንደታሰሩ ታውቋል።ተማሪዎቹ ጥያቄያቸውን በሰላም እያቀረቡ ባለበት ወቅት አድማ በታኝ ፖሊሶች አስላቃሽ ጪስ እንደተኮሱባቸውና አመጽ እንደተነሳ የአይን እማኞች ተናግረዋል። አድማ በታኝ ፖሊሶች አሁንም ከተማዋን ተቆጣጥረው በመንገድ ላይ የሚያገኙትን ወጣቶች ሁሉ እየተደባደቡ መሆኑን እንዲሁም ከ10 በላይ ትምህርት ቤቶች መዘጋታቸው ነዋሪዎች ተናግረዋል።

ይህ በእንዲህ አንዳለ በምእራብ ጎጃም ዞን በጃቢጠህናን ወረዳ የሆዳንሽ ቅዱስ ገብርኤል ቀበሌ ኗሪዎች የሆኑ ከአምስት ሺህ በላይ ነዋሪዎች ህገ-ወጥ ግንባታ በሚል ቤታቸው እንዲፈርስ የወጣውን ትዕዛዝ በመቀዋወም አደባባይ ወጥተዋል፡፡

የተቃውሞ ሰልፉ የተደረገው የወረዳው ከፍተኛ ባለስልጣናት ሚያዝያ 5 ፣ 2006ዓ.ም የቀበሌውን ህዝብ ሠብሰብው ከ808 በላይ ህገወጥ ቤቶች ይፈርሳሉ በማለት ያደረጉትን ንግግር ተከትሎ ነው።

"የመኖሪያቤት ጥያቄ የሰብዓዊ መብት ጉዳይ ነው" ያሉት ሠልፈኞቹ፣ ተቸግረን የገነባነውን ቤት በመንግስት ትዕዛዝ እንደዋዛ ሊፈርስ አይገባም ብለዋል፡፡

"መንግስት መመሪያውን በወቅቱ ባለማውጣቱና የወጣውን መመሪያ ተግባራዊ ባለማድረጉ በፈጠረው ስህተት ቤቶቻችሁ ሁሉ ይፈርሳሉ የሚል ትዛዝ ለምን አስተላለፈ?በበርሃ አረን፣ ከስለንና የደም እዳ ከፍለን የገነባነውን መኖሪያ ቤታችን ከላያችን ላይ ሲፈርስ መንግስት ለእኛ ለዜጎቹ ምን አማራጭ ይዞልን ነው? ልጆቻችንስ የት እናድርሳቸው? ሁሌ ተፈናቃዮችና ስደተኞች ከሆንን በነፃነት ቤት ሠርተን የምንኖርበት ሀገር ወዴት ነው? ህግ ወደ ኋላ ዞሮ በእኛ ላይ ተግባራዊ እንዲደረግ የተፈለገውስ ከምን አንፃር ነው? " የሚሉና ሌሎች ጥያቄዎችን ያነሱት ሠልፈኞቹ፣ ከዞንና ከወረዳ ባለስልጣናቱ ጋር ሳይግባቡ ተለያይተዋል፡፡ ህገወጥ ሠላማዊ ሠልፍ በማድረግ ሽብርና ሁከት ፈጥራችኋል በሚል በዞንና ወረዳ ባለስልጣናት ዛቻና የማስፈራራት ምላሽ ያልተደናገጡት ሠልፈኞቹ ፣ ጉዳዩ በህጋዊ መንገድ ትክክለኛ መፍትሄ እስከሚያገኝ እንታገላለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በሌላ ዜና ደግሞ በህገወጥ የጦር መሳሪያ ሠበብ መንግስት የሚያደርገው አሰሳ ደህንነታችንን አደጋ ላይ ጥሎታል ሲሉ የአማራ ክልል አርሶ አደሮች ተናግረዋል፡፡የኢህአዴግ መንግስት አማራ ክልል ላይ ባደረገው ተደጋጋሚ የጦር መሳሪያ ገፈፋ አርሶ አደሩ ባዶ እጁን መቅረቱን ጠንቅቆ እያወቀ ህገወጥ የጦር መሳሪያ ገፈፋ በሚል ዳግም ህዝብን ለምን እንደሚያንገላታ አልገባንም ያሉት አርሶ አደሮቹ ፣ በዚህ የመንግስት እንቅስቃሴ የተረጋጋ ህይወት መምራት አልቻልንም በማለት ተናግረዋል፡፡

የቋሪትና ጃቢጠህናን ወረዳ አርሶ አደሮች ህገወጥ የጦር መሳሪያ ገፈፋ በሚል ዘመቻ በተደጋጋሚ ሰለባ እንደሆኑና በደህንነት ስጋት ላይ መሆናቸውን ተናግረው፣ አሁንም የመጀመሪያዎቹ ሰለባዎች እኛ ሆነናል ሲሉ ህገወጥ የጦር መሳሪያ ቀብራችሁ ደብቃችኋል በሚል ቤታቸው የተቆፈረባቸው አርሶ አደሮች ተናግረዋል፡፡ ቀጣዩን ሀገር አቀፍ ምርጫ ተከትሎ የአማራ ክልል አርሶ አደሮች ያምፃሉ በሚል ስጋት በሶስት ዙር የጦር መሳሪያ ገፈፋ ሊካሄድ እቅድ እንደተያዘ ከኢህአዴግ ደህንነት አካላት የተገኘ መረጃ ያመለክታል። መሳሪያ ደብቃችሁዋል በሚል ሰበብ በአርሶ አደሮች ላይ ኢ-ሰብዓዊ የሆነ ደብደባና ግርፋት መፈፀሙን አርሶ አደሮች ለክልሉ ዘጋቢያችን ነግረዋታል።

## ወያኔ ቤታቸው የፈረሰባቸው የጎንደር ከተማ ነዋሪዎች ቁጣቸውን ገለጹ

በአለፈዉ ሳምንት መግቢያ አካባቢ ጎንደር ዉስጥ አዘዞ አይራ ቀበሌ አካባቢ ቤታቸው በጉልበት የፈረሰባቸዉ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የከተማዋ ነዋሪዎች በወያኔ አገዛዝ ላይ ያለቸዉን ቁጣ ሲገልጽ መከረማቸዉን ዘጋቢዎቻችን ከጎንደር በላኩልን ዜና ገለጹ። ብዙዎቹ ቤታቸዉ የፈረሰባቸዉ ነዋሪዎች ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ሜዳ ላይ የወደቁ ሲሆን፣ በዝናብና በፀሃይ እየተቸገሩ መሆኑንም ገልጸዋል። ባለፉት ሁለትና ሦስት አመታት ወያኔን ክፉኛ የተጠናወተዉ የቤት ማፍረስ አባዜ በብዙ አካባቢዎች ዜጎችን መድረሻ በማሳጣቱ አያሌ ዚትዮጵያዉያን ያለመጠጊያ በየቦታዉ መዉደቃቸዉ የሚረሳ አይደለም።

በነዋሪዎችና በፖሊስ መካከል መጠነኛ የሆነ ግጭት ተከስቶ እንደነበር ነዋሪዎች ተናግረዋል። አንዳንድ ነዋሪዎች ተስፋ በመቁረጥ በራሳቸው ላይ እርምጃ መውሰዳቸውን ነዋሪዎች ይገልጻሉ።በባህርዳር ከሳምንት በፊት ከ600 በላይ ህገ ወጥ የተባሉ ቤቶች ፈርሰዋል። ቤታቸው የፈረሰባቸው ነዋሪዎች ከፖሊስ ጋር በፈጠሩት ግጭት 2 ሰዎች ሲገደሉ፣ 9 ሰዎች ደግሞ በጽኑ ቆስለዋል። ከ20 በላይ ሰዎችም በእስር ላይ ይገኛሉ። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ህገወጥ ናቸው በሚል ከሚፈርሱ ቤቶች ጋር በተያያዘ ብዙ አቤቱታዎች እየተሰሙ ነው። መንግስት ከነዋሪዎች ጋር ተነጋግሮ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ፣ የጉልበት አማራጭን እየተጠቀመ መገኘቱ ለሰዎች ህይወት መጥፋት መንስኤ እየሆነ ነው በማለት አንዳንድ ወገኖች አስተያየቶችን ይሰጣሉ።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ኢትዮጵያ በየአካባቢዉ የሚታየዉ ዉጥረት እንደቀጠለለ ነዉ

ከወትሮው በፍጹም ባልተለመደ መልኩ በኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት የጉጅሌው ወያኔ ቁንጮ ሽመልስ ከማል ተነገረ የተባለው መግለጫ እንዳመለከተው በቤኒሻንጉል ክልል አሶሳ ዞን ሽርቆሌ ወረዳ ልዩ ስሙ ጠይባ በሚባለው አካባቢ ማክሰኞ ማለዳ 28 ሰዎችን ጭኖ ሲጓዝ በነበረውና የአገዛዙ ንብረት እንደሆነ በተነገረለት ተሽከርካሪ ላይ ማንነታቸው ያልታወቁ ታጣቂዎች ከፈቱት በተባለ ተኩስ ዘጠኝ ሰዎች ሲገደሉ፣ ሰባት ሰዎች ደግሞ ቀላልና ከባድ ጉዳት እንደደረሰባቸው ታውቋል፡፡ ግድያውን አስመልክቶ ዜናው በቀጥታ ከሚመለከተው የቤኒሻንጉል ክልል የፖሊስ ኮሚሽን ወይንም የአካባቢው ፖሊስ መነገር ሲገባው ይህንን አልፎ ከፋሽስቱ ወያኔ የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ተብየ መውጣቱ አግራሞትን የጫረ የግድያ ክስተት እንዳደረገው እየተነገረ ሲሆን ምናልባትም ከግድያው ጀርባ የነፍሰ በላው ህወሃት እጅ ሳይኖርበት አይቀርም የሚለው የበርካቶች ጥርጣሬ ሆኗል።

በተያያዘ ዜና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰላምና መረጋጋት ፈጽሞ በራቃት ጋምቤላም በተለያዩ አካባቢዎች የፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ታጣቂዎች እንደሰነዘሩት በተጠረጠረው ጥቃት አራት ሰዎች መገደላቸው የተዘገበ ሲሆን ከማቾቹም አንዱ በክልሉ የፋሽስቱ ወያኔ ከፍተኛ ተሿሚ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። በጋምቤላ በተለያዩ አካባቢዎች የተኩስ እሩምታ መስማት እየተለመደ መምጣቱን ያደረሰን የክልሉ ዘጋቢያችን ይህን ተከትሎ በክልሉ ከፍተኛ ውጥረት መንገሱ የታወቀ ሲሆን የክልሉ ህዝብ በከፍተኛ የደህንነት ስጋት ውስጥ መውደቁም እየተነገረ ይገኛል። በሌላ ዜና በጉጅሌው ወያኔ የበላይ አቀናባሪነትና በአካባቢው ግልገል የፋሽስቱ ካድሬዎች አቀጣጣይነት በጉጂና ቦረና ጎሳዎች መካከል በተለኮሰ ግጭት በርካታ ሰዎች መገደላቸውን በተለያዩ ጊዜያት መዘገባችን የሚታሰብ ሲሆን አሁንም ግጭቱ ዳግም ማገርሸቱን ተከትሎ ከ 5 ሰዎች በላይ መገደላቸውን ለማውቅ ተችሏል። በአሁኑ ሰአት ግጭቱ በተለያዩ ወረዳዎችና የገጠር ቀበሌወች በመዛመቱ ከፍተኛ ውጥረት በዞኑ መንገሱ እየተነገረ ሲሆን የሟቾች ቁጥርም ሳይጨምር እንደማይቀር ከአካባቢው የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

## ወያኔ የ2007 ምርጫ ማሸነፊያ ስትራቴጂ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ነፃ የምርጫ ቦርድ፤ ነጻ ሜድያ፤ ነጻ የፍትህ ተቋምና ለህዝብና ለአገር የቆመ መከላከያ ተቋም በሌለበት ቦታ ዉስጥ ወያኔ ሁሉንም ነገር እንደቤት ዉስጥ ዕቃዉ በሚቆጣጠርበት አገር ዉስጥ ለምን ምርጫዉን አሸነፋለሁ ብሎ እንደሚሰጋ ብዙዎች በመተቸት ላይ ናቸዉ። አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የፈለጉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁር በስልክ ለዝግጅታችች ክፍል እንደተናገሩት "ተቃዋሚዎች ወያኔን ማሸነፍ የሚችሉት ምርጫ ስለተካሄደ ብቻ አይደለም ካሉ በኋላ፤ ምርጫዉን ለማሸነፍና ወያኔን ከስልጣን ለማስወገድ የግድ ነፃ የምርጫ ቦርድ፤ ነጻ ሜድያና ለህገ መንግስት የሚገዛ መከላከያ ተቋም ያስፈልጋል ብለዋል። እንዚህ ሁሉ በሌሉበት ቦታ ሺ ግዜ ምርጫ ቢኖር ሁሉንም ምርጫዎች የሚያሸንፈዉ እንዚህን ተቋሞች የሚቆጣጠረዉ አካል ነዉ፤ ወይም በኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ወያኔ ነዉ ብለዋል።

ወያኔ የማሸነፊያ ስትራቴጂዎች በሚል ርእስ ከዘረዘራቸው ተግባራት መካከል "አርሶ አደሩንና አመራሩን የመዳበሪያ እዳ እፎይታ በ2006/2007 የመኸር ምርት ዘመን እንዳለ መንገር፤ ተቃዋሚችን ማንኳሰስ፣ በወያኔ ላይ ሊነሱ የሚያስቡትን እስከ ማግለል እንዲደርስ ማሰረዳት፣ ምርጫውን በ1 ለ 5 እንዴት ድምፅ እንደሚሰጡ ማስረዳት ወይም በሙከራ ማሳየት፣ ያለውን የፍትህ እና የልማት ችግር ወደ ፊት እንደሚፈታ በተስፋ መሙላት" የሚሉት ተጠቅሰዋል።ኢህአዴግ ባዘጋጀው የስትራቴጂ ወረቀት ላይ "የኢህአዴግ ትምህርት እና ስልጠና ከአመቱ መጀመሪያ ጀምሮ ህዝቡን ለመቀየር ቅርብ ናቸው ለተባሉ አርሶ አደሮች እና የቀበሌ አመራሮችን ‹‹ የኢህአዴግ ታሪክ››፤ የኢህአዴግ የልማት ስልቶች፤ የብሄርተኝነት ግንባታ፤ የሃገራችን የምርጫ ተሞክሮ፤" በሚሉት ርእሰ ጉዳዮች ላይ የሰጠው ስልጠና መሳካቱን ይዳስሳል።

የአማራ እና የኦሮምያ ክልሎችን ማመን እንደማይቻል የሚገልጸው ሰነዱ፣ "አመራሩ ኢህአዴግ ከወደቀ እስር ቤት እንደሚገባ ፤ የሚመጣው መንግስት አሁን በስልጣን ላይ ያሉትን የአመራር አካላት ቤተሰብም ጭምር ህይወት የሚያመሳቅል መሆኑን በማስረዳት፣' ኢህአዴግ ወይም ሞት' ብሎ በመነሳት ሊያስፈፅም እንደሚገባው ያትታል። የስራ መመሪያው ለከፍተኛ ጀማሪ አመራሮች በአስኳይ መውረዱን ለማወቅ ተችሎአል። የምርጫ ማስፈጸሚያ እቅድ ስልጠና የወረዳ እቅድ ከቀረበ በኋላ ተገምግሞ ሲያልቅ በዚህ መሰረት ቀበሌዎች ምርጫዎችን እንዴት ማሸነፍ እንደሚችሉ የቀበሌ እቅድ እንደሚያዘጋጁም ተገልጿል።

ለታችኛው አመራር ስልጠና የሚያገለግሉ መልእክቶች ተብለው ከተዘረዘሩት መካከል "ምርጫ 2007 የኢህአዴግ አሸናፊነት ይረጋገጣል፣ "ታላቁ መሪያችን ያስቀመጠልንን አደራ እናስቀጥላለን "፣ "በገጠር ቀበሌዎች የልማት፣ የዴሞክሲና የመልካም አስተዳደር ግቦቻችን በዘላቂነት ለማሳካት እንረባረባለን ፣ ፈጣን ልማት መልካም አስተዳደርና የህዝብ ተጠቃሚነት ተልእኮን የተገነዘበ ንቁ የቀበሌ አመራር የመፍጠር ተልእኳችን ይሳካል ፣ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመራችን አስተማማኝ ደረጃ መድረስ ብቁ የቀበሌ አመራር የመፍጠር ትግላችን ተጠናክሮ ይቀጥላል፣ መጭው ጊዜ ከኢህአዴግ ጋር ብሩህ ነው" የሚሉት ይገኙበታል። ከዚህ በተጨማሪ ግንቦት ሰባት ዉስጣችን ገብቷል ብሎ ኡኡታዉን የጀመረዉ ወያኔ የራሱን አባሎች በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ አስርጎ በማስገባት በተቃዋሚ ስም አሸንፊው እንዲወጡ ለማድረግ እየሰራ መሆኑም ታዉቋል።

## ወያኔ የረቀቁ የስለላ መሳሪዎችን ለመግዛት ብዙ ገንዝብ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የኢትዮጵያን የስልክና ኢንተርኔት አገልግሎት በብቸኝነት እያቀረበ ያለው የወያኔው ቴሌኮም መሆኑ ለችግሩ ከፍተኛ እገዛ ማድረጉን የጠቀሱት እነዚህ ሀገሮች የአውሮፓ ሀገሮች ብቻም ሳይሆን የአፍሪካ ሀገሮችም ይህን የወያኔ ድርጊት ማውገዝ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

ይህ ዘመናዊ የስለላ መሳሪያ በሀገር ውስጥ በቅርቡ የሞተውን የኦሮሚያ ቁንጮ ዓለማሁ አቶምሳን ጨምሮ በሌሎችም የወያኔ ከፍተኛ አመራሮች ላይ በጥቅም ላይ እንደዋለ ሲገለጽ በውጭ ደግሞ ባንዳንድ የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራሮች ላይ መገኘቱ አይዘነጋም።

## ሰማያዊ ፓርቲ ታላቅ ህዝባዊ የተቃውሞ ሠልፍ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሰላማዊ ፓርቲ በቤንሻንጉል ጉምዝ በህገ ወጥ መንገድ የተፈናቀሉ ኢትዮጵያውያን ወደ ቦታቸው በአስቸኳይ እንዲመለሱና ተገቢው ካሳ እንዲከፈላቸው እንዲደረግ በታዋቂው የአለማቀፍ ህግ ባለሙያ ዶ/ር ያዕቆም ሃይለማርያም አማካኝነት የመሰረተዉ ክስ ሃሙስ ሚያዝያ 9/2006ዓ/ም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስምንተኛ ፍትሃ ብሄር ችሎት ላይ መታየት እንደሚምር አንድ የሰላማዊ ፓርቲ ቃል አቀባይ ተናገሩ።

ቃል አቀባዩ ጨምረዉ አንደታገሩት ፓርቲው የቡለን ወረዳ ቀኑን ጠቅሶ ‹‹ስለምትፈናቀሉ ልቀቁ!›› ያለበትን ማስታወቂያና ማስጠንቀቂያዎች በመረጃነት መያዙ መሰረተዉ ክስ ታውቋል። ሰማያዊ ፓርቲ በአዲስ አበባ ሚያዚያ 19 የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ እንቅስቃሴ ጀምሯል። ኑ የተነጠቁ መብቶቻችንን እናስመልስ በሚል መሪ ቃል የሚካሄደው ሰልፍ የፖለቲካና የሰብአዊ መብቶች እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ለመንግስት በድጋሜ የሚቀርቡበት እንደሚሆን ፓርቲው በመግለጫው ጠቅሷል።

## ግድብ እያፈረሱ ጎርፍ መከላከል

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ግን ሊብራሊዝምን በጅምላ ማዉገዝ ነዉ እንጂ እንደዚህ አይነቱን መልካምና ጠንካራ ጎኑን አይነግሩንም ።

ወያኔ የቀለም አብዮት ብሎ ከሰሞኑ የለቀቀዉ ለዛቢስ ድራማ ምንም አይነት ምድራዊ ኃይል ማስቀረት የማይችለዉን ኢትዮጵያ ዉስጥ መሰረታዊ ለዉጥ የመካሄዱንና ወያኔም የመደምሰሱን እዉነታ ለማስቀረት የሚሞክር የፍርሀት ድራማ ነዉ። ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ ሠላምና መረጋጋት እንዲኖር ከፈለገና አገራችን ኢትዮጵያ ከተጋረጠባት የመበታተን አደጋ ተሰዉራ በዕድገት ጎዳና ወደ ፊት እንድትገሰግስ ከልቡ የሚመኝ ከሆነ ማድረግ ያለበት ሰዉ ሰዉ የማይሸት ድራማ እየሰራ መልቀቅ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ መብትና ነፃነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ማክበር ብቻ ነዉ። ወያኔ የኢትዮጵያን የፖለቲካና የኤከኖሚ መዋቅሮች ብቻዉን ተቆጣጥሮ፤ አገርን በዘረኝነት ፖሊሲ እየመራና ከሱ ጋር የማይስማሙ ዜጎችን ከቤታቸዉ ጎትቶ እያወጣ የሚገድል ከሆነ በዚያ በቀለም አብዮት ድራማ መግቢያ ላይ ሊያሳየን የሞከረዉ የጥይት ፍንዳታና የእሳት ቃጠሎ ኢትዮጵያ ዉስጥ የማይከሰትበት ምንም ምክንያት የለም። ስለዚህ ወያኔ እሩቅ አገር እየሄደ ስለ ዩክሬን፤ ስለ ጆርጂያና ስለ ኪርጊስታን መንግስታት ሙስናና አምባገነንነት ከሚነግረን እኛ በግልጽ የምናየዉን የራሱን ቆሻሻ ማራገፍ ወይም እሱ እራሱ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጀርባ ላይ ተጠራርጎ መርገፍ አለበት። ወያኔ ይህንን የማያደርግ ከሆነ ጥቁር ይሁን ነጭ ብርቱካናማ ወይም ጽጌረዳ ኢትዮጵያ ዉስጥ አብዮት መካሄዱ አይቀርም።